“ሕፃን፡ተወልዶልናልና፡ወንድ፡ልጅም፡ተሰጥቶናልና፡ አለቅነትም፡በጫንቃው፡ላይ፡ይሆናል፡ስሙም፡ድንቅ፡ መካር፤ኃያል፡አምላክ፤የዘላለም፡አባት፤የሰላም፡አለቃ፡ ተብሎ፡ይጠራል”።

ኢሳ፡ምዕ፡9፤6-7

<u>መድኅን፡ተወለደ</u>

የመድኃኒዓለም፡ክብር፡ለዓለም፡ተገለጠ፤
ለሰዎች፡መዳኛ፡ከአብ፡ዘንድ፡ተሰጠ፤
በቤተልሄም፡ተወልዶ፡ታሪክን፡ለወጠ።
በነብያት፡አባቶች፡በትንቢት፡ተነግሮ፤
ይኸው፡መጣ፡ዛሬ፡አክብሮ፡ቀጠሮ፤
በአማላጃችን፡በድንግል፡ላይ፡አድሮ።
የኢየሱስ፡መወለድ፡አስደንቆአቸው፤
ሰብአ፡ሰገል፡መጡ፡ወርቅ፡ዕጣን፡ይዘው፤
ኮከቡ፡መርቶአቸው፡መንፈስ፡ቀረቦአቸው፤
የአማኑኤል፡ፍቅር፡ከሩቅ፡ስቦአቸው።
የኢየሱስን፡ክብር፡ከዋክብት፡አሳዩ፤
እረኞችም፡አይተው፡ለሕፃኑ፡ዘመሩ፤
በዕውነት፡ተወለደ፡እያሉ፡አከበሩ።

መላዕክት፡በሰማይ፡የሚያመሰግኑት፤
ቅዱስ፡ነህ፡እያሉ፡ሰሙን የሚጠሩት፤
ሰዎችም፡አግኝተው፡በምድር፡ወደሱት፤
ክብር፡ልዕልና፡ኢየሱስ፡ነህ፡አሉት።
የአማኑኤልን፡ክብር፡እንስሳት፡አውቀው፤
በዛ፡በብርድ ወራት፡ተገኙ፡አብረው፤
ሙቀት፡እየሰጡ፡በትንፋሻቸው።
እሱ፡ሁሉ፡እያለው፡እንዳጣ፡ሰው፡ሆነ፤
ባንድ፡ጠባብ፡በረት፡እራሱን፡ወሰነ፤
ትህትናን፡ሊያስተምር፡የተከናወነ።
ሄሮድስ፡ሊያሰገድለው፡ሰዎችን፡ቢሰድም፤
ተልከው፡የሄዱት፡ቀሩ፡አልተመለሱም፤
በዕውነት፡የሱ፡ፍቅር፡ማንንም፡አይለቅም፤
ምንጊዜም፡አዲስ፡ነው፡ከቶ፡አይለወጥም።
የአዳምና፡የሔዋንን፡መርገም፡ለማጥፋት፤
ቤዛ፡ሆኖ፡ለማውጣት፡ከዲያብሎስ፡ግዛት፤
ይኸው፡ተወለደ፡የዓለም፡መድኃኒት፤
ሰውና፡መላዕክት፡ባንድ፡ላይ፡አዩት።
ዓለም፡ስትጨነቅ፡ኃጢአት፡ሞልቶባት፤

አንሰራፍቶ፡ይዞ፡ዲያብሎስ፡ሲመራት፤

መድኀኑ፡ክርስቶስ፡ተወለደላት፤

ለያዛት፡በሽታ፡ፈውስ፡ሊሆናት።

ኀይለመስቀል፡ተሰፋዬ

ለንደን